
RÉPUBLIQUE FRANÇAISE
*Liberté*
*Égalité*
*Fraternité*

INSTITUT NATIONAL DU CANCER


# ስለ HPV ወይም ሂዩማን ፓፒሎማቫይረስ ክትባት




ይህ ክትባት
ልጆቻችንን
ከHPVን ለመጠበቅ
በጣም ወሳኝ ነው።

## እድሜያቸው ከ11 ዓመት ጀምሮ ለሆኑ ሴት እና ወንድ ልጆች

ይህ ክትባት አስገዳጅ አይደለም እንጂ
በጥብቅ የተመከረ ነው።




ምስሎች ©SantéBD

# HPV የሚባሉት ምንድ ናቸው ?

HPV **ፓፒሎማቫይረስ** የሚባሉት የሰው ልጆችን የሚያጠቁ ቫይረሶች ናቸው።


HPV እጅግ ብዙ አይነቶች ናቸው።

ወደ 200 ገደማ የተለያዩ ፓፒሎማቫይረሶች አሉ።



**HPV በጣም ተላላፊ ናቸው።**

ማለትም ከአንድ ሰው ወደ ሌላ ሰው በቀላሉ ይተላለፋሉ። ብዙ ሰዎች በውስጣቸው እነዚህ ቫይረሶች ይገኙባቸዋል።



HPV ብዙ ጊዜ በመጀመሪያው የግብረ ሥጋ ግንኙነት አጋጣሚ የሚተላለፉ ናቸው። ኮንዶም ሙሉ በሙሉ ከHPV አይከላከልም።

አብዛኛውን ጊዜ ሰውነታችን እነዚህን ቫይረሶች ያጠፉቸዋል።

ሰውነታችን እነዚህን ቫይረሶች ካላጠፉቸው የሚከተሉትን ችግሮች ሊፈጥሩ ይችላሉ፤


- የቅድመ ካንሰር ቁስለት፥
ማለትም ግና ካንሰሩ ሳይከሰት፤

- ከንሰሮች፤

- የፈንጢጣ እና የመራቢያ አካላት ኪንታሮት፣
እነዚህ ኪንታሮቶች በፈንጢጣ እና በመራቢያ አካላት አካባቢ ይወጣሉ። እንደ ከባድ በሽታ ባይቆጥሩም ያሳምማሉ።




**ወንዶችም ሆነ ሴቶችም ሁሉም የሰው ልጆች የቅደመ ካንሰር ቁስለት፥ ካንሰሮች እና ኪንታሮት ሊከሰትባቸው ይችላል።**





**በየዓመቱ በፈረንሳይ አገር በHPV የሚፈጥር**
- 100 000 ያህል ኪንታሮት
- 6 400 አዳዲስ የካንሰር አጋጣሚዎች አሉ።

# የHPV ክትባት ጤናችንን የሚጠበቅ መድኃኒት ነው። ደህንነቱ የተረጋገጠ ነው።






**የHPV ክትባት ልጃችሁን ከሚከተሉት በሽታዎች ይከላከላሉ፤**




- የቅድመ ካንሰር ቁስለት እና/ ወይም
    - የማኅፀን ጫፍ ካንሰር
    - የሴት ብለት ካንሰር
    - የእምስ ካንሰር
    - የፊንጢጣ ካንሰር
- የፊንጢጣ እና የመራቢያ አካላት ኪንታሮት

**የHPV ክትባት ብቁ እና አደገኝነት የሌለው ነው።**

**በዓለም አቀፍ ከ100 ሚሊዮን ህጻናት በላይ ክትባቱን ተከትበዋል።**

# ልጄን በስንት ዓመቱ/ዓመቷ ላስከተበው/ ላስከተባት ?





## ክትባቱ ለሴቶች እና ለወንዶች ከ11 ዓመት እስከ 14 ዓመት ድረስ ይመከራል።

**ልጃችሁ በቶሎ ከተከተበ/ከተከተበች፤ ክትባቱ በተሻለ ሁኔታ ከብሽታዎች ይከላከላል።**

ከብሽታዎች ለመከላከል ክትባቱ **ሁለት ጊዜ መወሰድ** አለበት።

ከመጀመሪያው ክትባት 5 እስከ 13 ወራት በኋላ ሁለተኛውን እንዳትረሱ።





**ልጃችሁ ሁለት ክትባቶች በተመሳሳይ ጊዜ መወሰድ ይችላል/ትችላለች። ለምሳሌ ያህል፥**

- የHPV ክትባት፥
- ከ11 እስከ 13 ዓመት የሚወሰደው የdTcaP ማጠናከሪያ ክትባት።

dTcaP የተባለ የዲፍቴሪያ፥ የቴታኖስ፥ የአሴሉላር ትክትክ ሳል እና የፖሊዮ ክትባት ነው።


# ሌጄን በጊዜ ካላስከተብኩት/ካላስከተብኳት ምን ይሆናል ?




## ከ15 እስከ 19 ዓመት ድረስ ክትባቱን መወሰድ ይቻላል።

ያኔ ግን ክትባቱን ***ሦስቴ መወሰድ*** አፈላጊ ይሆናል።

ከሆነ የመጀመሪያው ክትባት ከተወሰደ 2 ወር በኋላ ሁለተኛውን ማስከተብ እና ከ6 ወር በኋላ ሦስተኛውን ማስከተብ እንዳትረሱ።



# ልጄን ሊከትቡት/ሊከተቧት የሚችሉት እነማን ናቸው ?



ሐኪም



የመድኃኒት ቤት ባለ ሙያ



አዋላጅ



ነርስ




በአቅራቢያችሁ ወዳለው የክትባት ማዕከል መሄድም ትችላላችሁ።


# ወጪው ስንት ይሆናል ?

የብሔራዊ ጤና መድህን ድርጅት (አሱራንስ ማላዲ) የክትባቱ ወጪው 65% ይመልስላችኋል።

ለምሳሌ ወጪው 100 ዩሮ ከሆነ፤ ድርጅቱ 65 ዩሮ ይመልስላችኋል። ቀሪው በተጨማሪ

መድህናችሁ ማለትም በሙቱኤል ሊመልስላችሁ ይችላል።





**ክትባቱ በሚከተሉት ሁኔታዎች በነፃ ይወሰዳል፤**

- ለሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (ኮሌዥ) ሰንኪኤም ክፍል ($5^{e}$) ተማሪዎች
- በምትኖሩበት ከተማ ወይም አውራጃ አንዳንድ የክትባት ማዕከሎች ውስጥ
- CSS ወይም AME የተባሉት የጤና መድህኖች ባለ መብት ከሆናችሁ።

# ልጃችሁ በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት (ኮለዥ) በሰንኪኤም ($5^{e}$) ክፍል ነው/ነች።

ፍቃዳችሁ ከሰጣችሁ ልጃችሁ በሚከተሉት ባለ ሙያዎች በት/ቤቱ ክትባቱን መወሰድ ይችላል/ትችላለች፥

- አንድ ሐኪም
- አንድ የመድኃኒት ቤት ባለ ሙያ
- አንድ አዋላጅ
- አንድ ነርስ




ልጃችሁ ሁለት ጊዜ ክትባቱን ይወስዳል/ትወስዳለች **የጤና ደፍተሩን/ደፍተሯን በእጁ/በእጇ መኖር አለበት። ክትባቱ በነፃ ይከተባል።**







ልጃችሁ የመጀመሪያ ክትባት ከሌላ ቦታ ከወሰደ/ከወሰደች ሁለተኛው በት/ቤት መወሰድ ይችላል/ትችላለች ።

**በ2023 የተከተቡ የ12 ዓመት ልጆች 400 ሺህ ናቸው።**

## ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት፥

ከሐኪማችሁ ጋር ተወያዩ ወይም
e-cancer.fr የተባለ ወብሳይት ላይ
ግቡ።

## ከልጃቹ ጋር ስለ ክትባቱን ለማውራት

በሚከተለው የኢንቴርነት ገጽ ግቡ
preventionenfant.e-cancer.fr

## በአጠቃላይ ስለክትባት ተጨማሪ ማረጃን ለማግኘት

ስለዚህ ጉዳይ SantéBD የተባለ ለልጆች
የተዘጋጀ ካርቱን አንብቡ። በነፃ በሚከተለው
የኢንቴርነት ገጽ ላይ ይገኛል።
www.santebd.org




ሥዕሎች: ©SantéBD

FALC በተባለ አሠራር የተጻፈ ነው።
ማለትም ለማንበብ እና ለመረዳት ቀላል
እንዲሆን በታሰበ አጻጻፍ ተዘጋጅቶ
የአዕምሮ ጉድለት ካላቸው ሰዎች ጋር
የታረመ። በESAT l'Envol (Unapei
34) ማኅበር የተዘጋጀ።

©ፋሲል አ ሊር የአውሮጳ ምልክት፥ ኢንክሉዚዮ እሮፕ። ተጨማሪ መረጃ በ www.easy-to-read.eu ላይ ይገኛል።

INCa - SIREN : 187 512 777 - ጁን 2024 - DEPVACCHPVFALC24.